## ስለ ምልጃ

### የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ስለ ምልጃ ምን ይላል?

ስለ ምልጃ አብዛኞቹ ነባር የወንጌላዊያን ቤተ-እምነት አባላት በሚገባ የሚያውቁ ቢሆንም ይህ ትምህርት የተዘጋጀው በተለይም አዳዲስ አባላት ስለ ምልጃ የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል እንዲያውቁና በዚህ ጉዳይ ከእግዚአብሔር ቃል ባፈነገጠ የትምህርት ነፋስ እንዳይደናገሩ እንዲረዳቸው በማሰብ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የወንጌል አማኞች ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በሚነጋገሩበት አጋጣሚ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ መልስ ለመስጠት የሚያግዛቸው እንዲሆን ነው፡፡

ምልጃና ማስታረቅ ጌታ ኢየሱስ ለኛ ካደረገውና ከሚያደርገው ነገር አንጻር በጣም ተዛማጅነት ያለው ነው፡፡

ምልጃ (Intercession):- ማለት አንድ ሰው በሌሎች ሰዎች ፈንታ ሆኖ ለልዩ ልዩ ጉዳይ ወደ እግዚብሔር ልመና በማቅረብ ምህረትና በረከትን ለማስገኘት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ሮሜ 8፡34፣ ሉቃ 22፡32

ጌታ ኢየሱስ ስለ እኛ ሲማልድ እንደ እኛው የሰው ስጋ ለብሶ በብዙ አሰቃቂና ከባድ መከራ ውስጥ ስላለፈበት የስጋ ለባሽ ድካም ምንም ሳይቀር ስለ ሚያውቀው እየራራልን ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ የሚረዳን ጸጋን ያስገኝልናል፡፡

መሸምገል/ማስታረቅ/አስታራቂ (Mediation/Mediator) ፡- በማስታረቅ ወቅት ከፍትህ አኳያ ጌታ ኢየሱስ በከፈለው ወደር አልባ ታላቅ ዋጋ፣ ለኛ የሚገባንን ቅጣት ሁሉ እርሱ ስለተቀበለና ዕዳችንን ሁሉ የከፈለ በመሆኑ እንዳይፈረድብን ነጻ በማድረግ ወደ እግዚአብሔር አብ የጸጋ ዙፋን በነጻነት መቅረብ ያስችለናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያው ምልጃ የተካሄደው በአብርሐም አማካይነት ለሰዶምና ገሞራ ነዋሪዎች ነበር፡፡ ሌሎች በብሉይ ኪዳን ዘመን ምልጃ ያካሄዱ ታዋቂ የእግዚአብሔር ሰዎች፡-

ኢዮብ.... ለልጆቹ፣ ለጓደኞቹ

ንጉስ ዳዊት፣.... ለእስራኤላዊያን፣ ከቤርሳቤህ ለወለደው ልጅ በታመመ ጊዜ፣

ንጉስ ሰለሞን፣.... ለእስራኤል ሕዝብ

ነህምያ፣..... ለእስራኤላዊያን፣ (ነህ 1፡4-11)፣

ነቢያት፣.... (ዳንኤል፣ ኤርሚያስ፣ ዲቦራ) ለእስራኤላዊያን ወደ እግዚአብሔር ምልጃ አቅርበዋል፣

የእስራኤላዊያን መሪዎች የነበሩት ሙሴና፣ ኢያሱ፡- ለእስራኤላዊያን ምልጃ አቅርበዋል

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ለተከታታይ ትውልድ እንዲማልዱ ለራሱ መርጦ በመለየት የመደበው ሌዋዊያን ካህናትን ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ የምልጃ ስራቸው ያከናወኑት በምድር በሕይወት ባሉበት ጊዜ እንጂ ሲሞቱ አገልግሎታቸው ስለሚያበቃ ሌላ ካህን በምትካቸው ይሾም ነበር፡፡

የእግዚአብሔር ቃል ለሚሾሙት ሊቀ-ካህናት መመዘኛ ያስቀመጠው መስፈርት የሚከተለው ነበር፡፡

1. ከሰዎች መካከል የተመረጠ (የሰው ዘር) መሆን አለበት፡፡ ከሌሎች ፍጥረታት ወይም ከመላዕክት እግዚአብሔር ለሰው ሊቀ-ካህናት እንዲሆን (እንዲማልድ)አላደረገም፡፡ ዕብ 5፡1-3፣ ዘሁ 17፡1-5-10፣ 18፡1-7፤ (ሌዋዊያን ለክህነት የተመረጡበት ምክንያት ዘጸ 32፡29፣ ዘኊ 8፡5-26)
2. ሊቀ-ካህናትን ከሰዎች መካከል የሚመርጠውና ሹመት የሚሰጠው እግዚአብሔር ራሱ ነበር፡፡ ዘሁ 17፡1-5፤ ዕብ 5፡4፣5-6፣9-10

3. ሊቀ-ካህናት በምድር ላይ በህይወት እየኖረ ያለ፤ የሚማልድላቸው ሰዎችን፣ ችግር ጉድለታቸውን ማየትና መስማት የሚችል እንጂ የማያያቸውና የማይሰማቸው ሙት ሰው መሆን አይችልም ነበር፡፡ ዕብ 7፡23-24-25፣ ዘጸ28፡1፣ ኢሳ 8፡19;

   ሊቀ-ካህናትና ካህናት ሲሞቱ በእነርሱ ምትክ ሌላ በምድር ላይ በሕይወት ያለ ሰው ይተካ የነበረው ለዚህ ነው፡፡ ሟቹ ሊቀ-ካህን በምድር የነበረው የቀድሞ ስራውን ይቀጥላል ተብሎ አይታሰብም/አይጠበቅም ነበር፡፡ በሟቹ ሊቀ-ካህን ቦታ የሚተካው፣ አብዛኛውን ጊዜ የሟቹ ሊቀ-ካህናት ልጅ (በዘር ሐረግ) ነበር፡፡ በሕይወት ካሉት ካህናት መካከል ዕጣ በመጣል ወይም በመንግስት አካላት/በነገስታት የተሾሙም ጥቂቶች ነበሩ፡፡ ነገር ግን ካናት ሁሉም በሚባል ደረጃ እግዚአብሔር ሊቀ-ካህን እንዲሆን ከመረጠው ከአሮን (ከሌዊ) ነገድ የሆኑ ሲሆኑ ሊቀ-ካህናት ሜኔላውስ/Menelaus/ ብቻ ከቢኒያም ነገድ ነበር፡፡

   በዚህ ምክንያት ንጉስ ሰለሞን ባሰራው ቤተ-መቅደስ አንዱ ሲሞት በሌላው በመተካት ያገለገሉ ሊቀ-ካህናት ቁጥር ብዛት 18 ሲሆኑ፣ ይህ ቤተ-መቅደስ የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነጾር ካፈራረሰው በኋላ በሜዶ-ፐርሺያው ኤምፓየር ሳይረስ (ቂሮስ) አማካይነት ተጀምሮ በተሰራው ቤተ-መቅደስ 60 ሊቀ-ካህናት፣ በጠቅላላው 78 ሊቀካህናት በየተራ ተሹመዋል፡፡ ነገር ግን በሮማው ኤምፓየር ገዢ የቫስፓሲያን ልጅ በጄኔራል ታይተስ አማካይነት በ70 ዓ.ም. ሁለተኛው ቤተ-መቅደስ በመፈራረሱ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእስራኤል የሊቀ-ካህናት ሹመት ተደርጎ አያውቅም፡፡
4. ደም ሳይፈስ ስርየት ስለሌለ ሊቀ-ካህናቱ ኃጢአት የሚያስተሰርይበት ደም ይዞ ወደ ቤተ-መቅደሱ ውስጠኛ ክፍል መግባት ነበረበት፡፡ የሊቀ-ካህናቱ ዋነኛ ስራ ደም በመርጨት ለራሱና ቤተሰቡ ለእስራኤላዊያንም ሁሉ ለታወቀና ላልታወቀ ኃጢአት ስርየት ማስገኘት ነበር፡፡ ዘሌ 16፡2-25፣ ዕብ 9፡6-7፣
   ሊቀ-ካህኑ በዓመት አንድ ጊዜ በሰባተኛው ወር 10ኛ ቀን ለራሱ፣ ለቤተቡና ለሕዝቡ ሁሉ የኃጢአት ማስተሰሪያ ካቀረበ በኋላ ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን በመግባት በስርየት መክደኛው ላይ የወይፈን ደም ይረጭ ነበር፡፡ ሌዋ 16፡14-16
   (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያማልድበት ምክንያት የራሱ ደም ይዞ (ያለ ደም ስርየት ስሌለ) ወደ ሰማያዊቱ ቅድስተ-ቅዱሳን በመግባቱ ብቻ ሳይሆን ኃጢአት ፈጽሞ የሌለበት በመሆኑ ነው፡፡ ዕብ 9፡12)
5. ዕድሜው 20 ዓመትና በላይ የሆነው ወንድ (ሴት ያልሆነ) መሆን ነበረበት፡፡ ዘሁ 8፡23-26
6. ለእስራኤል ሕዝብ አምላኩ ያዘጋጀውን መልካም ነገር ሁሉ መውረስ እንዲችል እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠውን ቃልና ሥርዓት ሁሉ እንዲጠብቁት ለህዝቡ መንገርና፣ በማብራራት ማስተማር… የሚያከናውን መሆን ነበረበት፡፡ ሌዋ 10፡11፣ ሚል 2፡4-7፣ ዘዳ 33፡10

የቀድሞዎቹ ካህናትም ሆኑ ማናቸውም የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ታላላቅና ታዋቂ የእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋዮች፣ ከሞቱ በኋላ ሊያማልዱ እንደማይችሉ የሚያስረዱ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች፡-

መክ 9፡4-6፣ "በሕያዋን መካከል ያለ ማንኛውም ሰው ተስፋ አለው፤ በሕይወት ያለ ውሻ ከሞተ አንበሳ ይሻላልና! [5] ሕያዋን እንደሚሞቱ ያውቃሉና፤ ሙታን ግን ምንም አያውቁምና፤ መታሰቢያቸው ይረሳል፤ ምንም ዋጋ የላቸውም። [6] ፍቅራቸው፣ ጥላቻቸው፣ ቅናታቸውም ከጠፋ ቈይቶአል፤ ከፀሓይ በታች በሚሆነው ነገር ሁሉ፣ ፈጽሞ ዕጣ ፈንታ አይኖራቸውም።" (ኢዮ 14፡10-12፣ 14፣ መዝ 88፡10፣ 11፣ ዕብ 9፡27፣ ኢሳ 63፡16፣ መክ 2፡16)

ኢሳ 8፡19፣ "ሰዎች፣ "የሚያነበንቡትንና የሚያሾካሹኩትን ሟርተኞችንና መናፍስት ጠሪዎችን ጠይቁ ቢሏችሁ፣ ሕዝቡ አምላኩን መጠየቅ አይገባውምን? በሕያዋን ምትክ ሙታንን መጠየቅ ለምን አስፈለገ?"

ዘሌ 19፥31፣ "እንዳትረክሱባቸው ወደ ሙታን ጠሪዎች ዘወር አትበሉ፤ መናፍስት ጠሪዎችንም አትፈልጉ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ (ያህዌ ኤሎሂም) ነኝ።"

ዘሌ 20፥6 "ወደ ሙታን ጠሪዎችና ጠንቋዮች ዘወር በማለት፣ በሚከተላቸውና ከእነርሱም ጋር በሚያመነዝር ሰው ላይ ጠላት እሆንበታለሁ፤ ከወገኖቹም ለይቼ አጠፋዋለሁ።" (ዘሌ 20፡27፣ ዘዳ 18፡9-13፣ 1ዜና 10፡13)

የሞቱ ቅዱሳን በሕይወት ላሉት ሊማልዱ ቀርቶ በሕይወት ያሉትም ቅዱሳን ጽድቅ ሁኔታ መጽሐፈ ኢዮብ ላይ እንደሚከተለው ይናገራል፡፡

ኢዮብ 15፡14-16፣ "ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ጻድቅስ ይሆን ዘንድ፣ ከሴት የተወለደ ምንድን ነው? [15] እነሆ፤ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ እንኳ አይታመንም፤ ሰማያትም በእርሱ ፊት ንጹሓን አይደሉም። [16] ታዲያ፣ ክፋትን እንደ ውሃ የሚጠጣ! አስጸያፊና ርኩስ ሰውማ እንዴት ይታመን!

መዝ 146÷3፣ "በገዦች አትታመኑ፤ ማዳን በማይችሉ ሥጋ ለባሾችም አትመኩ።"

ኤር 17÷5-7, እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "በሰው የሚታመን፣ በሥጋ ለባሽ የሚመካ፣ ልቡንም ከእግዚአብሔር የሚያርቅ የተረገመ ነው። በምድረ በዳ እንዳለ ቍጥቋጦ ይሆናል፤ መልካም ነገር ሲመጣ አያይም፤ ሰው በሌለበት በጨው ምድር፣ በምድረ በዳ በደረቅ ስፍራ ይቀመጣል። ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን፣ መታመኛውም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው።"

ኢሳ 2÷22 "እስትንፋስ አፍንጫው ላይ ባለች በሰው አትታመኑ፤ ከቶ ምን የሚበጅ ነገር አለው!"

ኢሳ 31÷1 "ወደ እስራኤል ቅዱስ ለማይመለከቱ፣ ከእግዚአብሔርም ርዳታን ለማይሹ፣ ነገር ግን፤ ለርዳታ ብለው ወደ ግብፅ ለሚወርዱ፣ በፈረሶች ለሚታመኑ፣ በሠረገሎቻቸው ብዛት፣ በፈረሶቻቸውም ታላቅ ብርታት ለሚመኩ ወዮላቸው!"

የሞቱ ቅዱሳን በዚህ ምድር ሰላለው ነገር ምንም እንደ ማያውቁ የሚያስረዱ ተጨማሪ ጥቅሶች፡-

ኢሳ 63÷16፣ "አብርሃም ባያውቀን፣ እስራኤልም ባያስታውሰን እንኳ፣ አንተ እኮ አባታችን ነህ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ አባታችን ነህ፤ ከጥንትም ቢሆን ስምህ "ቤዛችን" ነው።"

(በነብዩ ኢሳያስ ዘመን የነበሩ እስራኤላዊያን ታላቅ የእምነት አባቶች ቁንጮ የሆኑትን አብርሃምና እስራኤልን/ያዕቆብን እንኳ ከሞቱ በኋላ የእነርሱ ዘር የሆኑትን፣ በኋላ የተወለዱትን እስራኤላዊያን እንደ ማያውቋቸው መናገሩ፣)

ኢዮብ 14፡10-12፣...19-21 ሰው ግን ይሞታል፤ ክንዱንም ይንተራሳል፤ ነፍሱም ትወጣለች፤ ከእንግዲህስ የት ይገኛል? [11] ውሃ ከባሕር ውስጥ እንደሚያልቅ፣ የወንዝ ውሃም ጠፍቶ እንደሚደርቅ፣ [12] እንደዚሁም ሰው ይተኛል ቀናም አይልም፤ ሰማይ እስከሚያልፍ ድረስ አይነቃም፤ ከእንቅልፉም አይነሣም። ... [19] ውሃ ድንጋይን እንደሚቦረቡር፣ ጐርፍም ዐፈርን አጥቦ እንደሚወስድ፣ አንተም የሰውን ተስፋ ታጠፋለህ። [20] አንድ ጊዜ ፈጽመህ ትበረታለህ፤ እርሱም ያልፋል፤ ገጽታውን ትቀይራለህ፤ ትሸኘዋለህም። [21] ልጆቹ ቢከበሩ አያውቅም፤ ቢዋረዱም አያይም።

ስለ ሰዎች ብቃት ውስንነት ብቻ ሳይሆን ስለ ቅዱሳን መላዕክትም እንዲህ ይላል፡፡

ኢዮብ 4÷18 "እግዚአብሔር በአገልጋዮቹ ላይ እምነት ካልጣለ፣ መላእክቱንም በስሕተታቸው ከወቀሰ፤" (ስህተት የሚያገኝባቸው ከሆነ)...፣ ይላል፡፡ (ኢዮ15፡14-15)

ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክትን ለሰው ዘር ሁሉ እንዲማልዱ ኃለፊነት እንደ ሰጠ የሚያሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የለም፡፡

በምድር ላይ በሕይወት የሌሉ ቅዱሳን ሰዎችና የእግዚአብሔር መላዕክት ያማልዳሉ ብሎ ማመን፡-

1. የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው ጋር ተጻራሪ የሆነ የሀሰት ትምህርት መከተል፣ እግዚአብሔር የማይፈቅደውና ኃጢአት ነው እንጂ፣ ከእግዚአብሔር የሆነ መፍትሄ የሚያስገኝ አይደለም፡፡
2. በየትኛውም የዓለም ክፍል ውስጥ ያሉ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ብዙ ሰዎች በያሉበት ሆነው በአንድ ጊዜ በአጠገባቸው የሌለውን አንድ የሞተ ቅዱስ ሰውን ወይም ቅዱስ መልዓክን እርዳን፣ ጠብቀን፣ አድነን፣ መልካም ስጦታ ስጠን ብለው ሲጠይቁ፣ ሲያመሰግኑትና ሲያወድሱት ይሰማናል፣ ሲሰግዱለትም ያየናል

ብለው ማመን፣ የእግዚአብሔር ብቻ ባህርይ የሆኑት በሁሉም ስፍራ በአንዴ መገኘት ችሎታ፣ ሁሉን አዋቂነትና ሁሉን ቻይነት ችሎታ አላቸው ብሎ ማመን ነው የሚሆነው፣ ወይም እነዚህ ፍጥረታት ሆነው ሳለ፣ አምላክ/እግዚአብሔር ናቸው ብሎ ከመቀበል የተለየ አይደለም፡፡ ነገር አንድ አምላክ ያልሆነ የትኛውም ፍጥረት በአንድ ስፍራ ሆኖ በተለያየ የዓለም ክፍል ያሉ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በአንድ ጊዜ የሚጠይቁትን እርዳታ መስማት በፍጹም አይችልም፡፡
ቅድስት ማርያምን እንደ ምሳሌ ብንወስድ በምድር ላይ በሕይወት ሳለች ያደረገቻቸው አንዳንድ ነገሮች፣ በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ የመገኘት፣ የሁሉ አዋቂነትና ሁሉን ቻይነት መለኮታዊ ባህርያት እንዳልነበሯት የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያረጋግጣሉ፡፡

*ሉቃስ 2፡42-48፣ ""ልጁም ዐሥራ ሁለት ዓመት በሆነው ጊዜ፣ እንደተለመደው ወደ በዓሉ ወጡ።*
*[43] በዓሉን ከፈጸሙ በኋላ፣ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀረ፤ ወላጆቹ ግን*
*መቅረቱን አላወቁም ነበር። [44] አብሮአቸው ያለ መስሎአቸው፣ የአንድ ቀን መንገድ ተጓዙ፤ በኋላ ግን*
*ከዘመዶቻቸውና ከወዳጆቻቸው ዘንድ ይፈልጉት ጀመር፤ [45] ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም*
*ተመለሱ። [46] ከሦስት ቀንም በኋላ፣ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲያዳምጣቸውና ጥያቄ ሲያቀርብላቸው*
*በቤተ መቅደስ ውስጥ አገኙት፤...[48] ወላጆቹም ባዩት ጊዜ ተገረሙ፤ እናቱም፣ “ልጄ ሆይ፤ ለምን እንዲህ*
*አደረግኸን? አባትህና እኔኮ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር” አለችው።*
*ማር 3፡20-21፣ ከዚያም ኢየሱስ ወደ አንድ ቤት ገባ፤ እርሱና ደቀ መዛሙርቱ ምግብ መብላት እንኳ*
*እስኪሳናቸው ድረስ ሕዝቡ እንደ ገና በብዛት ተሰበሰበ። [21] ሁኔታውን የሰሙ ዘመዶቹም፣ “አእምሮውን*
*ስቶአል” በማለት ይዘውት ለመሄድ ወዳለበት መጡ።*

ከቤትዋ አብሯት የወጣ የራስዋ አንድ ልጅ ያለበት ስፍራ ማወቅ ስላልቻለች ይህን ያህል ቀናት ስትፈልግ የደከመች ሴት ያውም በምድር በሕይወት በሌለችበት ጊዜ፣ በምድር ላይ ያሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ በተለያየ የዓለም ክፍል ሆነው በአንድ ጊዜ አማልጅን ብለው የሚጠይቋትን ሁሉ ትሰማለች ብሎ መገመት፣ ምን ተአማኒነት ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የለውም፡፡ ደግሞም ጌታ ኢየሱስ በሚያስተምረው ትምህርትና በሚያደርጋቸው ተአምራዊ ሥራዎች ምክንያት ብዙ ሕዝብ እርሱን ፍለጋ እየመጣ ስለተከተለው፣ ዘመዶቹ/ቤተሰቦቹ አእምሮውን ስቶዋል (አብዶዋል) በማለት ይዘውት ወደ ቤታቸው በመሄድ ከሚሰጠው አገልግሎት ሊያቋርጡት መፈለጋቸው እርሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያገለገለ ያለ፣ አምላክ-ሰው መሆኑን ባለማወቃቸው ነው፡፡ ዘመዶቹ ከተባሉት ውስጥ ቢያንስ ቅድስት ማርያምና ባለቤትዋ ዮሴፍ መካተታቸው አይቀርምና፡፡
ደግሞም ምንም ማስረጃ የሌለው ነገር የሚናገሩ ሰዎች ቅድስት ማርያም እስከ ምድራዊ ኑሮዋ ፍጻሜ ድረስ ብቻ ሳይሆን አሁንም ድንግል ናት ይላሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡-
ማቴ 13፡55-56፣ "ይህ የአናጢው ልጅ አይደለምን? የእናቱስ ስም ማርያም አይደለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ስምዖንና ይሁዳ አይደሉምን? እህቶቹስ ከእኛው ጋር አይደሉምን?..."
ስለሚል 4 ወድሞች፣ እህቶቹስ? የሚለው የብዙ ቁጥር ቢያንስ 2 እህቶች እንደነበሩት ስለሚያሳይ ራሱ ጌታ ኢየሱስን ጨምሮ ቢያንስ ሰባት ልጆች መውለዷን ያስረዳል፡፡ ሰባት ልጆች የወለደች ሴት እንዴት ሁሌ ድንግል ልትሆን ትችላለች?
እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስን ከአንዲት እስራኤላዊት ድንግል ተጸንሶ እንዲወለድ ያደረገበት ምክንያት፣ ጌታ ኢየሱሰ ከኃጢአታችን የሚያድነን መሲህ ሆኖ ሲመጣ እርሱ ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው የዓለም ሕዝብ አዳኝ መሆኑን ከሚታወቅባቸው ልዩ ምክቶች (መሲሁ የመሆኑ ማረጋገጫ ማስረጃዎች) አንዱ እምዲሆን ነው እንጂ ማርያም እንደ አምላክ ተደርጋ እንድትታይ ለማድረግ አይደለም፡፡ ኢሳ 7፡10-14፤

3. ከዚህም ሌላ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ቅዱሳን ሰዎችና ቅዱሳን መላዕክት ጸሎቴንና ስዕለቴን ሰምተው ተዓምራዊ ስራዎች በመስራት ይረዱኛል ብሎ ማመንና ጸሎቴን ሰምተው መለሱልኝ በማለት ማመስገን፣ ማወደስ፣ ለእነርሱም መስገድ ወይም መስዋዕት ማቅረብ፣ የተሳሉትን ስዕለት መስጠት በማስከተል ወደ ጣዖት አምልኮ የሚያስገባ ተግባር በድፍረት እየፈጸሙ ያሉ ሰዎች ብዙዎች ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ

ውስጥ ስዕለት መሳልና የተሳሉትንም ስዕለት መስጠት ለእግኢአብሔር እንጂ ለየትኛውም እግዚአብሔረር ለፈጠረው ፍጥረት አድርጉ አይልም፡፡ (ዘዳ 23፡21፣1ሳሙ 1፡11፣ መዝ 50፡14፣ መክ 5፡4)

4. ይህ ዓይነቱ ድርጊት በየዕለቱ መልካም እያደረገልን ያለውን እግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክን የሚያስቀና ተግባር በመፈጸም ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኛ እያደረገ ለቁጣ የሚነሳሳው ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ለእርሱ የተገባውን ክብር፣ ምስጋናና ውዳሴ፣ ስግደትም ለሌሎች ያለ እርሱ ምንም ማድረግ ለማይችሉት ፍጥረታት ሲሰጥበት ቀናተኛ አምላክ ስለሆነ ይቀናል፡፡ ይህንኑ ከሚያስረዱ ጥቅሶች ጥቂቶቹ፤

*ዘዳ 6፡14-15፣ በዙሪያህ ያሉ ሕዝቦች የሚያመልኳቸውን ሌሎች አማልክት አትከተል፤ [15] ምክንያቱም በመካከልህ ያለው አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ቀናተኛ አምላክ (ኤሎሂም) ስለ ሆነ፣ በአንተም ላይ ቍጣው ስለሚነድ፣ ከምድር ገጽ ያጠፋሃል።*

*ዘጸ 20፡4-5፣ "በላይ በሰማይ ወይም በታች በምድር ካለው ወይም በውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች በማናቸውም ምስል ለራስህ ጣዖትን አታብጅ። [5] አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) የሚጠሉኝን ልጆች ከአባቶቻቸው ኀጢአት የተነሣ እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የምቀጣ ቀናተኛ አምላክ (ኤሎሂም) ነኝ፤*

*ኢሳ 42፥8፣ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜም ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፣ ምስጋናዬንም ለጣዖት አልሰጥም።" (ዘሁ 25፥6-11፣ ዘዳ 32፥16፣ 21)*

በአዲስ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ቃል በየትውልዱ ለሚኖር የሰው ዘር ይማልዳሉ የሚለው እነ ማንን ነው?

1. በብሉይ ኪዳን ዘመን ካህናት ወይም ነብያት ባይሆኑም ከእግዚአብሔር ጋር ያማረ ሕብረት የነበራቸው ሰዎች ለሌሎች ሰዎች ይማልዱ እንደ ነበረ፤ አሁንም በእኛ ዘመን በምንኖርበት አካባቢ በሕይወት ያሉ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ሕብረት ያላቸው (አኗኗራቸው እንደ እግዚአብሔር ቃልና እንደ መንፈስ ቅዱስ ምሪት ያደረጉ) ሰዎች፣ የአዲስ ኪዳን ሐዋሪያት፣ ነቢያት፣ አስተማሪዎች፣ ወንጌላዊያን፣ የቤተክርስቲያን መጋቢዎች (መሪዎች)፣ ማናቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑ የምልጃ አገልግሎት እንዲሰጡ እግዚአብሔር የጠራቸውና የመደባቸው አማኞች በሕይወት እስካሉ ድረስ ሊያማልዱ ይችላሉ፡፡ ኤፌ 6፡18፣ 1ጢሞ 2፡1፣ 2ጢሞ 1፡3
ደምሞም መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ በጌታ ኢየሱስ ያመነ እውነተኛ አማኝ፣ ካህን መሆኑን ያስረዳል፡፡
*1 ጴጥ 2፥9፣ "እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ፣ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ።" (1 ጴጥ 2፥5*)

2. ከበዓለ 50 ቀን ጀምሮ ወደ ምድር የመጣው ጌታ መንፈስ ቅዱስ ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ ምልጃ ነው፡ ፡
*ሮሜ 8፡26-27፣ እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል። [27] ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና።*
3. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን ካህናትን ተክቶ የሚማልድልን መሆኑ የሚያረጋግጡ ጥቅሶች፡-
*ሮሜ 8፡34፣ "ታዲያ የሚኰንን ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል።"*
*1ኛ ጢሞ 2፥5 "አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤"*

*ዕብ 7፡23-25፣ በአገልግሎታቸው እንዳይቀጥሉ ሞት ስለ ከለከላቸው፣ የቀድሞዎቹ ካህናት ቍጥራቸው ብዙ ነበር፤ [24] ኢየሱስ ግን ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ፣ ክህነቱ የማይሻር ነው። [25] ስለዚህ ስለ እነርሱ እየማለደ ሁል ጊዜ በሕይወት ስለሚኖር፣ በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።*

*ዕብ 10፡10-14፣ በዚህ ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ አማካይነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በቀረበው መሥዋዕት ተቀድሰናል። [11] ካህን ሁሉ በየዕለቱ ቆሞ አገልግሎቱን ያከናውናል፤ ኀጢአትን ማስወገድ ከቶ የማይችሉትን እነዚያኑ መሥዋዕቶች ዘወትር ያቀርባል። [12] ይህኛው ካህን ግን አንዱን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦአል፤ [13] ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ ይጠብቃል፤ [14] ምክንያቱም በአንዱ መሥዋዕት እነዚያን የሚቀደሱትን ለዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋል።* (በተጨማሪም ዕብ 9፡11-15፣ 22-28፣ *መመልከት ይቻላል*)

ዕብ 9፡11-12፣ "ክርስቶስ አሁን ስላሉት መልካም ነገሮች ሊቀ ካህናት ሆኖ በመጣ ጊዜ በሰው እጅ ወዳልተሠራችው፣ ከዚህ ፍጥረት ወዳልሆነችው ታላቅና ፍጹም ድንኳን ገባ። [12] የገባውም የፍየልንና የጥጃዎችን ደም ይዞ አይደለም፤ ነገር ግን የዘላለም ቤዛነት ሊያስገኝ የራሱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገባ።"

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ባለችው ቀድስተ-ቅዱሳን ሊማልድልን የገባው የገዛ ደሙን ይዞ ነው፡፡ ያለ ደም የኃጢአት ስርየት ስለሌለ የሞቱ ቅዱሳን በምናቸው ነው ኃጢአት የሚያስተሰርዩት?

ጌታ ኢየሱስ የቀድሞዎቹ ሊቀ-ካህናት ያሚሉት የነበሩትን መስፈርቶች ያሟላ ብቻ ሳይሆን አምላክ ሆኖ ሳለ ራሱን ዝቅ በማድረግ ሰው የሆነ፣ ምንም የሃጢአት እንከን የሌለበት፤ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛትና ፈቃድ ሁሉ ሙሉ በሙሉ የፈጸመ፤ ኃጢአታችንን የሚያስተሰርይ የራሱ ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የገባ፤ ከሊቀ ካህናት ሁሉ እጅግ የላቀ ሊቀ-ካህናታችን ነው፡፡ ጌታ ኢየሱሰ ክርስቶስ ያኔ በምድር ላይ ሆኖ ያገለግል በነበረበት ዘመን፥ አሁንና ወደፊትም የዓለም ፍጻሜ እስከ ሚሆን ድረስ የሊቀ-ካህናት (የምልጃ) ስራ እንደ ሚሰራ የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል፡፡

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ በሰማይ በከበረ ዙፋኑ ላይ ብቻ የሚኖር ሳይሆን ሰማይ ሰማያት ሊይዙት የማይችሉ፣ ስፍራ የማይስነው ታላቅ አምላክ በመሆኑ በጌታ ኢየሱስ ባመኑት ሰዎች ሁሉ ውስጥ እንደሚኖር የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጠል፡፡ አምላካችን የሩቅ አምላክ ብቻ ሳይሆን ከማንም ከምንም ይልቅ ቀርቦን በውስጣችን እየኖረ እያለ፣ እያየንና እየሰማን ሌሎች ፍጥረታት አማላጆች እንዲሆኑን መጠበቅና መጠየቅ፣ ለእግዚአብሔር የተገባውን ምስጋና፣ ውዳሴና ስግደት ለእነርሱ መስጠት ኃጢአት ከመሆኑም በላይ በውስጣችን የሚኖረው አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እኛ ስናጎነብስ ከእኛው ጋር እንዲሰግድላቸው በማድረግ አዋረድነው ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል በሚየያምኑት ሰዎች ሁሉ ውስጥ እንደ ሚኖር የሚያሳዩ ማስረጃዎች፡-

*ዮሐ 14፥23፣ "ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱ እንመጣለን፤ ከእርሱም ጋር እንኖራለን::"*

*2ኛ ቆሮ 13፥5፣ "በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ:: ከፈር የወጣችሁ (የሳታችሁ) ካልሆነ በስተቀር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን?" (ሮሜ 8፡10፣ ገላ 2፡20)*

*1ኛ ቆሮ 3፥16፣ "እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን?" (1ዮሐ 4፡13)*

*ቆላ 1፥27 "ለእነርሱም እግዚአብሔር የዚህ ምስጢር ክብር ባለጠግነት በአሕዛብ መካከል ምን ያህል እንደሆነ ለማሳወቅ መረጠ፤ እርሱም የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ ነው::"*

ማናቸውም የቀድሞ የአዲስ ኪዳን ታዋቂ የእግዚአብሔር አገልጋዮች፣ በአሁኑ ዘመን ትውልድ መታወቅ የቻሉት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም መምጣትና ከእርሱ በሆነው ጸጋ ምክንያት ብቻ ነው። እነርሱ በነበሩበት ትውልድ መካከል እንኳ ታዋቂ የሚያደርጋቸው መንፈሳዊም ሆነ ምድራዊ በረከትና ችሎታ የነበራቸው ሳይሆን በሕብረተሰቡ ውስጥ ከዝቅተኛው መደብ የሆኑ ነበሩ። እርሱ የሰው ዘርን ለማዳን ወደ ዓለም ባይመጣና ያገለገሉበትን የጸጋ ስጦታ ባይሰጣቸው ኖሮ ስማቸውን እንኳ ፈጽሞ አናውቃቸውም ነበር። ደግሞም እነዚህ ማናቸውም ታዋቂ የወንጌል አገልጋዮችና የእግዚአብሔር ሰዎች የዳኑትና የዘለዓለም ሕይወት ማግኘት የቻሉት በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በማመናቸው ነው እንጂ በራሳቸው ማንነት ብቃትና ጽድቅ ፍጹምነት አይደለም። ያም ሆኖ በተሰጣቸው ጸጋ ሕይወታቸውን እንኳ መስዋዕት እስከ ማድረግ ድረስ ይህን ወንጌል ለእኛ ለማስተላለፍ የደከሙት ድካምና የከፈሉት ታላቅ ዋጋ በማየት፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ ባኖረውና በገለጠው ጸጋ ምክንያት፣ እኛ ስለ እነርሱ የምናስበው, የምንናገረውና ያለን ስሜት ወይም የምናደርገውን ባያውቁም፤ በሕይት ሳሉ ስላደረጉት ነገር በመልካም አርዓያነታቸው እናከብራቸዋለን፣ እንወዳቸዋለን፣ እንጂ ልንመካባቸውም፣ ልናመልካቸውም በጭራሽ አይገባም።

እግዚአብሔር እርሱ የፈጠረው ሕዝብ በራሱ በእግዚአብሔር እንጂ በሌላ በማንም እንዲመካ አይፈልግም። ስለዚህ ነው በአዲስ ኪዳን ለዘለዓለም የሚኖሩት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ጌታ መንፈስ ቅዱስን ስለ እኛ እንዲማልዱ ያደረገው።

ኤር 9፡23-24፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ “ጥበበኛ በጥበቡ አይታበይ፤ ኀያልም በኀይሉ አይመካ፤
ሀብታምም በሀብቱ አይኵራራ፤24 የሚመካ ግን፣ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንሁ በማወቁና፣ በምድር
ላይ ምሕረትን፣ ፍትሕንና ጽድቅን የማደርግ መሆኔን በመረዳቱ፣ በዚህ ይመካ፤ እኔ በእነዚህ ነገሮች፣
እደሰታለሁና፤” ይላል እግዚአብሔር።

1 ቆሮ 1፡26-31፣ "ወንድሞች ሆይ፤ በተጠራችሁ ጊዜ ምን እንደ ነበራችሁ እስቲ አስቡ። በሰው
መስፈርት ከእናንተ ብዙዎቻችሁ ዐዋቂዎች አልነበራችሁም፤ ብዙዎቻችሁም ኀያላን አልነበራችሁም፤
ብዙዎቻችሁም ከትልቅ ቤተ ሰብ አልተወለዳችሁም። 27 ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር
ዘንድ የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔር ብርቱዎችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ደካማ ነገር
መረጠ። 28 እግዚአብሔር የተከበረውን እንደሌለ ለማድረግ፣ በዚህ ዓለም ዝቅ ያለውንና የተናቀውን
ነገር፣ ቦታም ያልተሰጠውን ነገር መረጠ፤ 29 ይኸውም ማንም ሰው በእርሱ ፊት እንዳይመካ ነው።
30 በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ
ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኖአል። 31 እንግዲህ፣ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ
ነው፤ “የሚመካ በጌታ ይመካ።”

መለኮታዊ ክብር፣ ስግደትና አምልኮ ለእግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ይሁን! አሜን!!!

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.